# አንቺው ታመጪው…እንዲሉ ካመጣሽውማ

## ከመድረኩ ደርግ ይሻላል!!

## ክፍል ሁለትና የመጨረሻ

**ዮናስ 12-11-14**

በክፍል ሁለት ትርክታችን የሚጀምረው ዶክተር መራራ ለሰንደቅ የሰጡትን ቃል እንደወረደ በመመልከት ነው። •

‹‹ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ሃይሎች ያላለፉት የታሪክ ፈተና፣ ማሸነፍ ያልቻሉት የታሪክ ፈተና በተለይም ተባብሮ መሥራት ፣ አቅም ገንብቶ የመሥራት፣ ልዩነቶችን አቻችሎ አብሮ የመስራት፣ ተባብሮ ገዢውን ፓርቲ  የመግፋት ፖለቲካው አሁንም ድረስ ያላለፉት ታሪክና ፈተና ሆኖ ቀጥሏል፡፡ አሁንም አላለፍነውም፡፡ እንዲያውም ከ97 ጋር ሲተያይ ደከም ብለን የምንታይበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡ ስለዚህ ከአሁን ጀምሮ የተቃዋሚው ሃይሎች ቁጭ ብለው አሰላስለው ያለንበትን ሁኔታ መመልከት ተገቢ ነው፡፡ በተለይ ትግሉ ወደፊት እንዲገፉ የተሻለ ውጤት ለማምጣት ይህን የታሪክ ፈተና ለማለፍ ካልቻልን የትም መድረስ አንችልም፡፡ ኢትዮጵያም የትም መሄድ አትችልም፡፡ እየተቋሰሉ ፣እየተጣሉ እየተጠላለፉ ፣ በተተበተበ ፖለቲካ ውስጥ እየዋዠቁ መኖር ለራሳችንም ሆነ ለሃገራችን የተሻለ ሥራ እየሰራን እንዳልሆነ ይሰማኛል የበለጠ ወደ ኋላ ቀርተናል፡፡››

ሰዎች፥ ከዶ/ር መራራ ደርግ ከኢህአዴግ የመሻሉ ሚስጥር ከተተረከለት ሰንደቅ ጋዜጣ ላይ ከተወሰደው እና ከላይ ከተመለከተው ነጥብ ላይ የተሰመሩባቸውን ሃረጋት በደንብ አስተውሉ፡፡ አስተውሎታችሁም በጽሁፌ መግቢያ አካባቢ ከተዘረዘረውና ከብዙ በጥቂቱ ምርጫ 97ን እና 2002ን ካስታወስንበት አኳያ እንዲሆን አድርጉ፡፡ ለመሆኑ አብሮና ተባብሮ ከመሥራት ጋር ተያይዞ እንዲተባበሩ ከሚጠበቁትና ፣ዶ/ር መራራ

እንዲያንሰላስሉ ከጠየቋቸው ፓርቲዎች በላይ ሆነው በስብሰቡ ውስጥ አባያ የነበረው ማን ነው?።

ምርጫ 97ም ከላይ በተመለከተው አግባብ ተቃዋሚዎቹ ሊታወሱ የሚችሉት በአመጽ እና በዜሮ ድምር ፖለቲካ ከመሆኑ አግባብ ‹‹ከምርጫ 97 አኳያ ደከም ብለን የምንታይበት ሁኔታ ነው ያለው›› ማለትስ ምን ማለት ነው?። የተደፈኑትን የአመጽ ቀዳዳዎችና የተዘጉ በሮች አሁንም በሃይል እና በጉልበት እናስከፍት ማለትም እንደሆነ ጥርጣሬ አይገባንም፡፡

እነርሱ ስላልተባበሩ "ኢትዮጵያ የትም መድረስ  አትችልም" ማለትስ ምን ማለት ነው?፡፡ በመቋሰል እና በማቋሰል፤ በመጣላትና በማጣላት፤ በመጥለፍና በማጠላለፍ እንዲሁም በተተበተበ ፖለቲካ ከፓርቲዎችም በላይ ማን እንደ ዶ/ር መራራ አለና ነው፡፡

ስለሆነም ከላይ የተመለከተውና ከዶ/ር መራራ ትርክት ተቆንፅሎ ከቀረበው ፅንሰ ሃሳብ ጥቅል ትርጓሜ፤ እንዲሁም በትዝታ ወጋችንም ሆነ ከላይ በተመለከቱት ሁለት የሠንደቅ ጋዜጣ ጥያቄዎችና የዶ/ር  መራራ ምላሾች አኳያ የዶ/ሩ አሁንም ገዢ ሥርዓቱን ያለ ምርጫ ፖለቲካ ከነነገደ ኀበዜ ጋር በተመሰጠረ ሴራ በአመጽ ለማስወገድ እንተባበር የሚል ነው፡፡የሴራውንም ንድፍ ፕሮፌሰር በየነ ጴርሰው እንደመጡ ሁለት አመት በማያውቁት ፓርቲ ላይ የተሰጣቸውን ስልጣን ታሳቢ አድርገን መጠርጠር አስቀድሞ ለመጠንቀቅ ይበጃል።

ይህ ደግሞ ቢያንስ  ምንም ዓይነት የመድበለ ፓርቲ ሥርዓት ባልነበረበት ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ሲያጨማልቀው ከነበረው ደረጉ የከፋና ስለሃገራችን ዲሞክራሲያዊነት እስከነ ችግሮቹም ቢሆን የተዘረጋውን መስመር ለማደባየት የመቋመጥ አምባገነናዊ አመለካከት ነውና ካመጡት አልቀረ ከደርግም የባሱ መሆናቸውን እንድንነግራቸው የሚያስችለን አስተሳሰብ ነው፡፡

በተተበተበ ፖለቲካ የመዋዠቅ ጉዳይን ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር አያይዘው ያነሱልን እና ከላይ ተመልከትን ያሂስናቸው ዶ/ር መራራ ይልቁንም መዋዥቃቸውን እና አቋም የለሽ የመሆናቸውን ሚስጢር የገለጡት ደግሞ ከአረቡ ዓለም የጸደይ አብዮት ጋር ተያይዞ ጋዜጣዋ ላነሳችላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ ነው፡፡

ትዝ ይላችሁ እንደሁ ዶ/ር መራራ የአረቡ አለም አብዮትን ሲያንቆላለጳሱ እና የታህሪርን አደባባይ ለመስቀል አደባባይ ሲያልሙ መክረማቸው ይታወቃል፡፡ ለዚህ ህልማቸውም ቅዠት የመሆኑን ፍቺና መሰረት የሌለው አስተሳሰብ መሆኑን በተለያዩ አስረጂዎች እያጣቀስን ስንሞግታቸው በሰጡን የዘለፋ ምላሾቻቸውም እናስታውሳቸዋለን፡፡ ዛሬ ደግሞ ደርሰው በግብጽ የተካሄደውን አመጽ "የገመድ ጉተታ ነው" ሲሉ ከገለጹት በኋላ የኛዎቹንና ዶ/ሩ ለትብብር የሚጠሯቸውን ተቃዋሚዎችም የታህሪርን አደባባይ  የገመድ ጉተታ ፖለቲካ በመስቀል አደባባይ መሻት መልሶ ለገመድ ጉተታ የሚዳርግ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ በግብጽ እንደሆነው ከአመጽ በኋላና በድንገቴም ቢሆን ይህ ሥርዓት ቢወገድ ሊመራ የሚችል ተቃዋሚ አለመኖሩን እና እኛ ስንል የከርመነውን ይናገራሉ፡፡ እንደው ጠዋት ማታ" አንድነት" ስለተባባሉ ቀውስ ማቆም የማይቻል እንደሆነም በተመሳሳይ አልሰማ ብለውን እንዳልነበር ዛሬ ይተረኩልናል፡፡

የማግለልን፣ እና የፍረጃን ፖለቲካ ተቃውመው ለትብብር የሚሰብኩትና ከላይ በተመለከተው አግባብ ጥሪ ሲያስተላልፉ ዶ/ር መራራ በተለይም አንድነት የተሰኘውን ፓርቲ ነጥለው የአማራ ልሂቃን ስለመሆኑና እድልም ገጥሞት ወደስልጣን ቢመጣ ኢትዮጵያን  የሚያጠፋ መሆኑን ይመሰክራሉ፡፡ ምስክርነቱ እና ቢያንስ ቀደም ብለው ሲሞግቱን በነበረው ጉዳይ ላይ መተማመናችን እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ግን ጉዳዩን በጥልቀት ካየነው አሁንም የመጠላለፍ ፣የመቋሰል፣ የማግለል ፖለቲካን በሥልት እያራመዱና ከላይ በተመለከተው አግባብ ከዚያ አስከፊ ሥርዓት ነጻ ወጥቶ ዛሬ ላይ በልማቱም ሆነ በዴሞክራሲው መስክ ቁንጮ በመሆን ላይ ያለውን የኦሮሞ ህዝብ እንደተበደለ በማስመሰል የማጫረስ ፖለቲካ ቁማራቸው እንደሆነ ሊሰመርበት ይገባል፡፡ስለሆነም ይህ አስተሳሰብ በጅምላ ከሚፈርጀው ደርግ የከፋና መጨረሻው ከደርጉም የከፋ የእርስ በእርስ እልቂት የሚያበቃ የጥላቻ ፖለቲካ መሆኑም ተሰምሮ መድረኩ ከደርጉ የከፋ የመሆኑም ሚስጢር ሊገለፅና አጽንኦት ሊሰጠው ይገባል፡፡እርሳቸው እንዳሉት የትምክህት ሃይሉም ሆነ እርሳቸው የሚያራምዱት የጥበት አስተሳሰብ በተመሳሳይ ኢትዮጵያን የሚበታትን አደጋ ሊፈጥሩ ይችላሉ እንጂ እርሳቸው የሚቆምሩበት የአማራ ልሂቃን ወይም የትምክህቱ ስብስብ ለብቻውና ከእርሳቸው የጥበት ሃይል ጋር ካልተደባለቀ የሚፈጥረው አንዳች ነገር እንደሌለም ሊረዱት ይገባል፡፡

በገገርው ግንባር ውስጥ በተደረጉ ውስጠ ዴሞክራሲያዊ ትግሎች በስብሰው በመገኘታቸው በዚህም ተቆርጠው ሊጣሉ የሚገባ መሆኑ ታምኖበት የተጣሉትን (እነ አልማዝ መኮ ዶ/ር ነጋሦና ሃሰን አሊ) ስለ ኦሮሞ ህዝብ በደል መገለጫ ሆነው ዶ/ሩ ትርክት ላይ መስፈራቸው በራሱ (እነርሱም ውስጠ ዴሞክራሲያዊ ትግል የሌላቸውና እንደ አንድ ድርጅት ተጠያቂነት በሌለበት የዘቀጠ መንገድ ለሚጓዘው ደርጅታቸው መግሪያ ሊያደርጉት ሲገባ) የአምባ ገነንነታቸውን ጥግ የሚያሳይና ለ17 አመታት ኢሠፓን ሲመራ ከነበረው ደርግም በላይ ወደ ስልጣን ቢመጡ ከደርግ የከፉ ስለመሆናቸው የሚያጠይቅ ነው፡፡ በእርግጥም ዶ/ር መራራና መድረካቸው ከደርጉም ስለመከፋታቸው የሚያረጋግጡን ሌሎች ጉዳዮችም በትርክታቸው ላይ ሰፍሯል። እነዚህም ህግ መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለመናድ ነፍጥ ካነገቡትና በሽብርተኝነት በመገለጻቸው ሽብርተኛ ተሰኝተው በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤትም ሆነ በህግ አቋም ስለተያዘባቸው ኦነግን ለመሰሉ ሃይሎች በትርክታቸው ላይ በተለሳለሰ እና በሚያስነቃ መልክ እውቅና መስጠታቸው ነው፡፡

ከዚህ ባሻገርና ግን ደግሞ በጥቅሉ ‹‹ ዲሞክራሲያዊ የሚባለው ብሄራዊ መግባባት መፍጠር ሲቻል ብቻ ነው፡፡ ሃገራችን እንዴት ትመራ? ምን ዓይነት ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ያስፈልገናል? የፖለቲካ መቻቻል የብሄር ብሄረሰቦች መብት ? የፌዴራሊዝም አይነት ? ቁጭ ተብሎ መነጋገር ስትችል ነው፡፡ ይህ ባልሆነበት ሁኔታ ማንኛውም አይነት ለውጥ ቢመጣ ወደ ተፈለገው ዲሞክራሲያው ሥርዓት አይደረስም›› ሲሉ የገለጹት ቁጭ ብለንና ተነጋግረን የዛሬ 20 ዓመትት መልስ የሰጠናቸውን ጥያቄዎች ውድቅ ማድረጋቸው ሥለ ሥልጣን መቋመጥ ከምርጫ ባሻገር ያስቀመጡት ጸረ ዴሞክራሲያዊ የመፍትሄ ሃሳብ ነው።

ስለሆነም ከላይ የሰፈሩትና ስለ ዜሮ ድምር ፖለቲካ እንዲሁም ስለ ደርግ ናፍቆትና ከደርግም በላይ ለመሆን ተብለው የተዘረዘሩ እና በጥያቄ መልኩ ከደ/ሩ የተሰጡ አስተያየቶችን መመለስና በሁነኛ አስረጂዎች ማሄስ ያስፈልጋል። ይልቁንም እስከ ዛሬ የተደረጉትን እና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገለጫ የሆኑትን የምርጫ ሂደቶች ሁሌ ከሚያላዝኑበት የሰብአዊ መብት፣ ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ ጋር በማያያዝ ከላይ በተመለከተው አግባብ ሲያንኳስሱና አሁንም በማንኳሰሳቸው ቀጥለው "አማራጭ ስላጣን "ስላሉት የምርጫ ሁነት ጋር አያይዘን ገገርው ፓርም ሆነ በገገርው ፓርቲ የሚመራው መንግስት ከደርጉ የመብለጡን ብቻ ሳይሆን የማይገናኙ የመሆናቸውን ምስጢር የሚያጠይቁ ነጥቦችን

በማንሳት ምርጫ 2007 ታሳቢ አድርገው በዶ/ሩ ለተወረወሩት ጦሮች አክሻፊ ምሶችን በማጠየቅ ይህን ፋይል እንዘጋለን፡፡

የሰብአዊ መብቶች መከበር፣ የህግ የበላይነት፣ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ፣እንዲሁም ሰላምና ልማት የማይነጣጠሉና ተደጋጋፊ የሆኑ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ መሰረቶች መሆናቸው ይታወቃል፡፡ ይህም ሲባል- የዲሞክራሲ ጽንሰ ሀሳብ መሰረቱ የህዝብ ራስን በራስ ማስተዳደርና በራሱ ጉዳይ ላይ መወሰን ነው፡፡

በዚህ መብት ለመጠቀም የዲሞክራሲያዊ ስርዓት መኖርን የግድ ይላል ።ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ደግሞ ከዴሞክራሲያዊ መንግስት ውጭ አይታሰብም። ዴሞክራሲያዊ መንግስት የሚመሰረተው ደግሞ በዴሞክራሲያዊ ምርጫ ብቻ ነው። ለነጻ ፍትሃዊና፣ ዲሞክራሲያዊ ምርጫ መኖር ዋነኛ መሰረቱ ደግሞ የዜጎች ሰብአዊ መብቶች በሁለንታናዊ መልኩ መከበር መሆኑ አያጠያይቅም፡፡

በመሆኑም ዜጎች የመምረጥና የመመረጥ ሰብአዊ መብታቸውን በመጠቀም ወቅቱን ጠብቆና በተወሰነ ጊዜ በቋሚነት በሚካሄድ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ በመሳተፍ ለህዝብ ፍላጎት ተገዥነትና ተጠያቂነት ያለው ዴሞክራሲያዊ መንግስትን ወደ ሥልጣን መምጣት ወሳኝ ድርሻ ይኖራቸዋል ማለት ነው፡፡

ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ማለት በቋሚነት የሚታወቅና በየጊዜው የሚካሄድ ነጻ ፣ፍትሃዊ፣ ድምጽ በሚስጥር የሚሰጥበት፣ ትክክለኛና ተዓማኒነት ያለው፣ የአንድ ሀገር ዜጎች በድምጻቸው ወኪሎቻቸውን ወደ ስልጣን የሚያመጡበት ወይም ከስልጣን የሚያነሱበት ዴሞክራሲያዊ ህዝበ ውሳኔ መሆኑ የምርጫ ስርአት ሀሁ ነው፡፡

ስለዚህ ምርጫ እነመራራ ለመረረ ጉዳይ ቢሹትም ምርጫ የህዝብ ሉዓላዊ የስልጣን ባለቤትነትን ማረጋገጫ ብቻ ነው የሚሆነው። የህዝብ ድምጽ የመንግስትን የስልጣን ምንጭነት ማሳያ እንጂ ስልጣን የጠማቸው ተማክረው የሚቀራመቱት እንዳልሆነ ግልጽ ሊሆን ይገባል። ከላይ በተመለከተው መርሆ እስካሁን ያከናወናቸው ሃገር አቀፍና አካባቢያዊ ምርጫዎች የዴሞክራሲያዊ መንግስት አሰራር ግልጸኝነትና ተጠያቂነት ማረጋገጫዎች እንጂ እነ መራራ እነደሚሉት ተራ የቁማር ትዝታ አይደም። ይልቁንም በኢትዮጵያ ታሪክ ዜጎች በሃገራቸው ጉዳይ ውስጥ በቀጥታ መሳተፍንና መወሰንን

ያረጋገጡበት ነው። ይህ ደግሞ የዜጎች ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ስለመከበራቸው መገለጫ እንጂ እነ መራራ ለሚሉት "ከደርግም የከፋ ስርአት"ማሳያ አይሆንም ፡፡

በመሆኑም ወቅቱን ጠብቆ በየጊዜው በሚካሄድ ነጻ ፍትሃዊና ትክክለኛ ምርጫ አማካኝነት በመንግስት አስተዳደር መሳተፍ የዜጎች የማይገሰስ ሰብአዊ መብት መሆኑን አውቀን በግንቦት ወር 2007 ዓ.ም በሚካሄደው ብሄራዊ ምርጫ ሁለችንም መንጫጫትን ሳይሆን አማራጭን መሰረት ያደረገ የነቃ ተሳትፎ ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡

እነ መራራ የሚያወድሱትን የደርግ ምርጫ ስርአት በተመለከተም ምርጫ በማንኛውም ጊዜና ቦታ ሊደረግ ይችላል በሚለው ተጠየቅ ማሄስ ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ከሌላና እየተናፈቀ ከሚገኘው ደርጉ ምርጫ የሚለይበት መርሆዎች ስላሉት ነው፡ ፡ ከእነዚህም መካከል ዋና ዋናዎቹ የዜጎች በመንግስት አስተዳደር መሳተፍ፣የዜጎች መምረጥና የመመረጥ መበት መከበር መረጋገጥ ፣በሕዝባዊ አገልገሎቶች እኩል ተጠቃሚ /ተደራሽ/ መሆን ፣የዜጎች በሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች እኩል ተጠቃሚ መሆን፣ በተለይም ሴቶች ከወንዶች ጋር እኩል መሆናቸው መረጋገጥ፣ የራስን ጉዳይ በራስ የመወሰን መብታቸው መረጋገጥ፣ የዜጎች በሀገራቸው ጉዳይ የሚያደርጉት ፖለቲካዊ ተሳትፎ መረጋገጥ እንዲሁም የሌሎች መሰረታዊ መብቶችና ነጻነቶች ማለትም ሃሳብን በነፃነት የመግለጽ፣ መረጃ የማግኘትና የማሰራጨት የመሰብሰብና መደራጀት፣ የመዘዋወር ከማናቸውም ተጽእኖ ጫና ነጻ መሆን ወዘተ መብቶች መከበርና መረጋገጥ መርሆች ላይ የተመሰረተ መሆኑ ከብዙው በጥቂቱ እና ዋና ዋናዎቹ ሲ ሆኑ በነዚህ መርሆዎች የሚገለጸውና ለነዚህም መከበር የተጋው ኢህአዴግ እንጂ እየተናፈቀ ያለው ደርግ አለመሆኑ ሊሰመርበት ይገባል ።ስለሆነም ይህንኑ አውቀን እና ተገንዝበን መጪው ብሄራዊ ምርጫ ነጻ ፍትሃዊ ትክክለኛና ዲሞክራሲያዊ ይሆን ዘንድ ከላይ ለተመለከቱ መርሆዎች ተግባራዊነት ሁላችንም መረባረብ ይገባናል፡፡

በሃገራችን በመጪው ግንቦት ወር ለአምስተኛ ጊዜ የሚካሄደው ብሄራዊ ምርጫ ነጻ ፍትሃዊና ዲሞክራሲያዊ እንዲሆን ይጠበቃል፡፡ ስለሆነም ከምርጫው ነጻና ፍትሃዊነት ጋር ተያይዞ ዶክተር መራራ ላሄዷቸው ጉዳዮች ለመሆኑ ምርጫን ነጻ ነው የሚያሰኙ መስፈርቶች ምን ምንድናቸው? የሚሉትን ጉዳዮች በማየት መልስ መስጠት ይቻላል።

በምርጫ የሚገለጽ የህዝብ የራሱን ጉዳይ በራሱ የመወሰን በሀገሩ ጉዳይ የመሳተፍ መብት መኖር ፣መራጮችን ከማናቸውም ተጽእኖ ጫናና ማስፈራራት ነጻ የሚያደርግ ሕዝባዊ የፖለቲካ ተሳትፎ ድባብ/ ሁኔታ መኖር፣ በመሰረታዊ አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት በተለይም ሃሳብን በነጻ የመያዝ መረጃን በነጻነት ማግኘትና የማሰራጨት፣ የመሰብሰብና የመደራጀት፣ ከአድልዎ ነጻ የመሆንና በእኩልነት የመታየት መብቶች መከበር፣ ጉድለቶችም ካሉ ይህን በአግባቡ የሚዳኙ ገለልተኛ አካላት በተለይም የነጻ ፍ/ቤቶች መኖር፣ የፀጥታ ኃይሎች ከወገንተኝነት የፀዱና ገለልተኛ ሆነው ምርጫው በሰላም ይካሄድ ዘንድ ጸጥታ የማስከበር ሙያዊ ሚናቸውን ብቻ በምርጫ አስፈጻሚዎች አመራር ስር ሆነው መወጣት፣ የመምረጥ እና የመመረጥ መብት አጠቃቀምንና ሰፊ ፖለቲካዊ ተሳትፎን የሚገድቡ በስራ ላይ ያሉ ሕጎች ካሉ መለወጥ ወይም መታገድ፣ የሕዝብ ፖለቲካዊ ፍላጎት በተሟላ መልኩ የሚገለጽበት የምርጫ ሥርዓት ሲኖርና ይህም የመንግስት ሥልጣን ምንጭ ሆኖ ማገልገል መቻል የመሳሰሉት ናቸው።

ለሁሉም ወገኖች ያለአድልዎ የሚያገለግሉ የምርጫ ሕጎች ሲኖሩና በትክክል ስራ ላይ ሲውሉ- ለመራጭነት ወይም ዕጩ ተወዳዳሪነት የሚያበቃ መመዘኛን የሚያሟላ ዜጋ ሁሉ በእኩልነት ያለአንዳች ገደብ የሚያሳትፍ ሁሉ አቀፍ ምርጫ ሲሆን(universal suffrage) በተለያዩ መስፈርቶች በተለይም በዘር ጾታ ወዘተ ላይ ከተመሰረተ አድልዎ የጸዳ ምርጫ (non-discriminatory positive measures) ሲወሰዱ፣ አንድ ሰው አንድ ድምጽ በሚል መርህ ላይ የተመሰረተ ሆኖ እያንዳንዱ ድምጽ እኩል ዋጋ ኖሮት የመራጭን ፍላጎት በተሟላና በትክክል የሚያንጸባርቅ ሲሆን (equal suffrage) የምርጫ ሂደቱ (ከምዝገባ እስከ ቆጠራና ሪፖርት ማድረጊያ) ከማጭበርበርና ከአድልዎ ነጻ መሆኑን ለማረጋገጥና ቅሬታዎችን ወዲያውኑ ለማስተነገድ የሚያስችሉ ተቋማዊ፣ ሕጋዊና ቴክኒካዊ ዋስትናዎች ሲደረጉ ምርጫውን ለማሳካት የተዘረጉ አሰራሮች የትኛውንም ወገን በተለየ ሁኔታ ከመጥቀም ወይም ከመጉዳት ነጻ ሲሆኑና በተለይም ሚዲያዎች ለሁሉም ዕጩዎችና ፓርቲዎች ፍትኃዊ በሆነ መልኩ ተደራሽ ሲሆኑ፣ በመጨረሻም በሀገሪቱ ህግ መሰረት በምርጫው በቂ ድምጽ ያገኘ ተወዳደሪ የመንግስት ሥልጣን ሲይዝ ነው ምርጫ ተደረገ የሚባለው እንጂ በመራራ የብሄራዊ እርቅ ስሌት ድምጽን ሲከፋፈሉ አይደለም፡፡

ድምጽን በሚስጥር መስጠት ምርጫን ነጻና ፍትሃዊ በማድረግ ረገድ ትልቅ ድርሻ እንዳለውም ይታወቃል፡፡ድምጽ በሚስጥር መስጠት ሲባል ደግሞ በተለየ ሁኔታ በሌላ ሰው

እንዲረዱ ከተወሰነው ውጭ የድምጽ አሰጣጡ በቀጥታ ራሱ መራጩ በድምጽ መስጫ ጣቢያው በአካል በመገኘት ከመስጠት ውጭ የቡድን የድምጽ አሰጣጥ አለመኖሩ አንዱ ነው፡፡

በቅድሚያ ከተወሰነውና በይፋ ከሚታወቀው ድምጽ መስጫ ክልል ውጭ ሌላ ምርጫ ጣቢያ አለማቋቋም፣ የድምጽ መስጫ ጣቢያውና ሣጥኑ የድምጽ መጭበርበርንም በሚያስወግድ አኳኋን መደራጀትና የድምጽ መስጫ አካባቢና የዕጩ ተወዳዳሪ ምልክቶች የሁሉንም መራጮች ፍላጎት የዕውቀት ደረጃና ሁኔታ (ያልተማሩ አቅመ ደካሞች አካል ጉዳተኞች ከአካባቢያቸው ርቀው የሚኖሩ ሰራተኞች፣ ተማሪዎች፣ የመከላከያ ሰራዊት አባላት ወዘተ) ከግምት ያስገቡ መሆኑም መረጋገጥ አለበት።

መራጭን ከማናቸውም ተጽእኖ እና ጫና ነፃ የሚያደርግ ድምጽ በሚሰጡር የሚሰጥበትና ውሳኔውንም ማለትም ደምጹን ለማን እንደሰጠ የማይታወቅበትና እንዲያሳውቅም የማይገደድበት ሥርዓት የተመቻቸ መሆንንም ይጠይቃል። በድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ምርጫ አስፈጻሚዎች ሥልጣናቸውን ያለአግባብ እንዳይጠቀሙ ለማድረግ ለመራጮች የሚሰጡ ማብራሪያዎችና ሊቀርቡላቸው የሚችሉ ጥያቄዎችም ቀደም ብለው ተወስነው የተለዩና የሚታወቁ ብቻ መሆንን የሚያካትት መሆኑን ማወቅ ለመምረጥ ከተዘጋጀነው ሁሉ ይጠበቃል፡፡

ምርጫ እኩልነት፣ የሁሉ አቀፋዊነትና የድምጽ ሚስጢራዊነት የጠበቀ አካሄድ ተከትሎ የተፈጸመ (genuine procedure) ከመሆን በተጨማሪ ለህዝቡ አማራጮች በበቂ ሁኔታ ሲቀርብለትና በተለይም ምርጫው ትርጉም ባለው ፓርቲዎች ውድድር ላይ የተመሰረተ ሲሆን ህዝቡ ስለሂደቱ ስለዕጩዎች፣ ስለ ፓርዎችና ይዘው ስለቀረቡት አማራጮች በቂ ዕውቀት ኖሮት በግንዛቤ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ ሊሰጥ ይቻለዋል እንጂ አስቀድሞ በሚደረገ ከአማራጭ የዘለለ መንጫጫት የምርጫው ፍትሃዊነትና ዴሞክራሲያዊነት ላይ አንዳች ፋይዳ አይኖረውም።

ውጤቱ በትክክል የሕዝብን ፍላጎት ያረጋገጠ ሆኖ ሲገኝ፣ በቂ ቁጥር ላላቸውና ገለልተኛ ለሆኑ የውስጥ ወይም ውጭ ታዛቢዎች ምርጫውን የመታዘብና ትክክለኝነቱን የማረጋገጥ እድል ሲሰጥ፣ ወቅቱን ጠብቆ በተወሰነ ጊዜ በቋሚነት በሚካሄድ ምርጫ አስቀድሞ በተለየና የሚታወቅ አካሄድ ላይ ተመስርቶ በአንድ ምርጫ ክልል አብላጫ ድምጽ ያገኘ

ተወዳዳሪ አሸናፊ የሚሆንበት ሥርዓት ሲዘርጋና በዚሁ መሰረት ሥልጣኑን ወደ አሸናፊው በማስተላለፍ ሁሌም የመንግስት ስልጣን ሕጋዊ መሰረቱ የህዝብ ድምጽ መሆኑን ማረጋገጥ ሲቻል (genuine effect) ምርጫውን ትክክለኛ እንደሚያደርገው ይታወቃል።

ይህ ደግሞ በተጨባጭ የተከናወነው እነመራራ በሚናፍቁትና በሚያሞግሱት የደርጉ ዘመን ሳይሆን እነመራራ በሚያማርሩት ግን ደግሞ መራራ ተበደለ የሚሉት ኦሮሚያን ጨምሮ የሁሉም ክልል ህዝቦች በሚያወድሱት በሚጠብቁትና በጋራ በገነቡት ኢህአዴግ ነው። ስለሆነም ለቀጣዩ ብሄራዊ ምርጫ ትክክለኛነትና ተዓማኒነት እንዲሁም ሰላማዊነት የነመራራን ጭብጥ አልባ ማማረሮች ትተን አማራጭን መሰረት ላደረገ መራጭነት መረባረብ የሃገራችንን ዴሞክራሲያዊነት ከምንመኝ ዜጎች ሁሉ ይጠበቃል ፡፡